“አንደበቱን፡ሳይገታ፡ልቡን፡እያሳተ፡እግዚአብሔርን፡የሚያመልክ፡የሚመስለው፡ማንም፡ቢኖር፡የእርሱ፡አምልኮ፡ከንቱ፡ነው።” ያዕቆብ፡ምዕ፡1፧26

## አንደበት

ሠይጣን፡በመሪነት፡የሚቆጣጠረው፧
መርገም፡ብቻ፡ማግኛ፡በረከት፡ያልሆነው፧
አንደበተ-እሳቱ፡ብዙ፡ኃጢአት፡አለው
አቃጥሎ፡ጨርሶ፡አመድ፡የሚያደረግ፡ነው።
በእግዚአብሔር፡አምሳያ፡ስንፈጠር፡ገና፧
ለማመስገን፡ነበር፡እያልን፡ገናና፧
የእስራኤል፡አምላክን፡የሰጠውን፡መና።
አማኑኤል፡ቸሩ፡የከበረበት፡
በምድር፡እያለ፡የታወቀበት፧
ዋና፡መገናኛው፡ያስተማረበት፧
ነበረ፡አንደበቱ፡ሰው፡ያዳነበት።
በቁስል፡ቢመታ፡ንብረቱ፡ቢጠፋ፧
ሚስቱ፡ከድታው፡ብትሄድ፡ልጆቹ፡ቢሞቱ፧
መቼ፡አጉረመረመ፡ኢዮብ፡የሰው፡ብርቱ፧
መልካም፡ይሁን፡አለ፡በገዛ፡አንደበቱ።
እስጢፋኖስ፡ዲያቆን፡ወጣቱ፡ሰማዕት፧
መከራን፡አፅንተው፡ግፍ፡ቢያደርጉበት፧
በመልካሙ፡አንደበት፡ይቅር፡አለበት፧
ሞቱ፡ሕይወት፡ሆኖ፡ፅድቅ፡አገኘበት።
ጴጥሮስ፡የተባለው፡የጌታ፡ሐዋርያ፧
ነበረው፡አንደበት፡ወንጌልን፡ማብሰሪያ፧
ከአምላክ፡ያገኘው፡ፀጋ፡መቀበያ።
ሰለስቱ፡ደቂቅን፡ከእሳት፡ያወጣቸው፧
የእግዚአብሔርም፡መልአክ፡የተላከላቸው፧
በንጉሡ፡ፊትም፡ሞገስ፡የሰጣቸው፧
አምላክ፡ያድነናል፡ሆኖ፡ነው፡ቃላቸው።
በወንጀል፡ተከሶ፡ታስሮ፡የነበረው፧
ጥጦስ፡አመፀኛው፡አምላክን፡አወቀው፧
በመስቀል፡ላይ፡ሳለ፡ተአምር፡ስላሳየው፧
በዚህን፡ጊዜ፡ወንበዴው፡ዞር፡በማለት፧
ጌታ፡ሆይ፡አስበኝ፡አለ፡በእምነት፧
የገነትም፡ደጃፍ፡ተከፈተለት።
ዘመድ፡ከዘመዱ፡ሲጣላ፡የታየው፧
አይንህ፡ለአፈር፡ብሎ፡የተረጋገመው፧
እሳት፡አንደበቱ፡አጋይቶ፡ጥሎት፡ነው።
አንደበተ-ምላጭ፡እውነት፡የለበትም፧
ሰውን፡ከሰው፡ጋራ፡አያስተዛዝንም፧
ሁሌ፡ተናጋሪ፡መሆን፡አይበጀንም፧
ሌላውን፡ለመስማት፡ጊዜን፡አይሰጠንም።
አንደበተ-እሳቱ፡ሲቃጠል፡ያስፈራል፧
በአጭር፡ጊዜ፡ውስጥ፡ሁሉን፡ያዳርሳል፧
ከአድማስ፡አድማስ፡ዘልቆ፡በቅፅበት፡ይገድላል።
ያልታደለ፡አንደበት፡ሲሄድ፡ያለልጓም፧
ወላፈኑ፡አቃጥሎ፡ሰውን፡አያስጠጋም፧
እያገረሸበት፡ቤቱ፡ጠርቶ፡አይጠራም።

አንደበተ-ልዝብ፡በጎ፡የማይወጣው፤
ለሰው፡ፀር፡በመሆን፡መንገዱን፡የዘጋው፤
አምላክ፡ተቆጥቶ፡በመአት፡እንዳይመታው፤
ዲያብሎስ፡ተሽክሞ፡ሲያል፡እንዳይጥለው፤
ዛሬ፡ተመልሶ፡አንደበቱን፡ይግዛው።
በአንደበታችን፡ከምንጠፋ፡ዛሬ፤
ምን፡አለበት፡ለአምላክ፡ብናቀርብ፡ዝማሬ፤
በህይወት፡ዘመናችን፡እንድናገኝ፡ፍሬ።
ጥበበኛ፡ማነው፡አስተዋይ፡የሆነ፤
በእሳት፡አንደበቱ፡ፈፅሞ፡ያዘነ፤
ይምጣ፡ኤልሻዳይ፡ቤት፡ሁሉን፡እየጣለ፤
ያገኛል፡አንደበት፡የተከናወነ፤
የማይፋጀውን፡ህይወት፡ብቻ፡የሆነ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ
ለንደን